የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ስምንተኛ ዓመት ቁጥር ፴፮
አዲስ አበባ—ሰኔ ፳፭ ቀን ፲፱፻፺፬

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

8th Year No. 36
ADDIS ABABA-2nd July, 2002


## ማውጫ


አዋጅ ቁጥር ፪፻፹፰/፲፱፻፺፬ ዓ·ም
የብሔራዊ የግብርና ግብዓት ባለሥልጣን ማቋቋሚያ
አዋጅ ........................................................ ገጽ ፲፱፻፯


## CONTENTS


Proclamation No. 288/2002
National Agricultural Input Authority
Establishment Proclamation .................... Page 1907


### አዋጅ ቁጥር ፪፻፹፰/፲፱፻፺፬
### ብሔራዊ የግብርና ግብዓት ባለሥልጣንን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

ለሀገሪቱ ዕድገትና ልማት መሠረት የሆነውን የግብርናውን ክፍለ ኢኮኖሚ ምርትና ምርታማነት በማሳደግ ፣ አርሶ አደሩና አርብቶ አደሩ ከዚሁ ተጠቃሚ መሆኑን ማረጋገጥ አስፈላጊ በመሆኑ ፤

የግብርናውን ዘርፍ ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ የተለያዩ የግብርና ግብዓቶችን በጥራት ፣ በዓይነትና በበቂ መጠን በማምረትና ፣ በማቅረብ በዘርፉ ለተሰማራው ተጠቃሚ እንዲዳረስ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ ፤

በግብርና ግብዓት ማምረት ፣ ማቅረብ ፣ ሥርጭትና ንግድ ተግባር ላይ እንዲሳተፉ የግል ባለሀብቶች ፣ መንግሥታዊ ድርጅቶችና ሌሎችም አግባብ ያላቸውን በማበረታታት የዘርፉን የሥራ ሂደት ማጠናከር በማስፈለጉ ፤

የግብርናውን ምርትና ምርታማነት በማሳደግ ቀጣይነት ያለው ልማት በሀገሪቱ ለማረጋገጥ የግብርና ግብዓቶችን በሥርዓት አስተባብሮና አቀናጅቶ መምራት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ፤

በአጠቃላይ የአገሪቱን ወቅታዊና ዘላቂ የግብርና ልማት ፍላጎት ለማሟላት የሚያግዙ የግብርና ግብዓቶች አግባብ ባላቸው ሕጎችና ደንቦች መሠረት ጥራታቸው ተጠብቆ በወቅቱ እንዲቀርቡ በመከታተልና ቴክኖሎጂዎችንም ለማስፋፋት የሚያስችል አቅምና ክህሎት የመገንባት ፍላጎት በመኖሩና ይህንንም ሥራ የሚያስተባብርና የሚከታተል አካል ማቋቋም በማስፈለጉ ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭/፩/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል ።

### *PROCLAMATION NO. 288/2002*

### *A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF THE NATIONAL AGRICULTURAL INPUT AUTHORITY*

WHEREAS, increased production and productivity of the agricultural sector is necessary to the growth and development of the country, and to ensure that farmers and pastoralists benefit therefrom;

WHEREAS, the production of various of high quality agricultural inputs in sufficient variety, quantity and the supply of same is important to users in raising the production and productivity of the agricultural sector;

WHEREAS, it is necessary to strengthen the input sub-sector by encouraging the participation of the private sector, government organs, and others in the production, supply, distribution and trade of agricultural input;

WHEREAS, it has been found essential to manage agricultural inputs in a systematic, coordinated and integrated manner for increased agricultural production and productivity in order to ensure sustainable development in the country;

WHEREAS, it has become necessary to establish an Authority, in accordance with relevant laws and regulations, that ensure timely and quality supply of inputs; and build capacity, knoweldge and skills to promote input technologies in order to fulfill the current and long term requirements of the country;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:


ያንዱ ዋጋ 2·30
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ·ሣ·ቁ· ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

፩· <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "የብሔራዊ የግብርና ግብዓት ባለሥልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፪፻፹፰/፲፱፻፺፬" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

፪· <u>ትርጓሜ</u>

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፣

፩· "የግብርና ግብዓት" ማለት የግብርናውን ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ ለገበያ የሚቀርቡ የዕፅዋት ዘር ፣ ማዳበሪያና ፀረ-ተባይ ናቸው ፣

፪· "የዕፅዋት ዘር" ማለት እውን ዘር ፣ አኩራች ፣ ቅጥፍ ተክል ፣ ወይም ለዕፅዋት ማራባት የሚያገለግል ማንኛውም የተክል ክፍል ወይም አካል ነው ፣

፫· "ማዳበሪያ" ማለት አንድ ወይም ከአንድ በላይ ለተክል ምግብነት የሚውሉ ንጥረ ነገሮችን የያዘ ፣ በተፈጥሮ የሚገኝ ወይም በፋብሪካ የተዘጋጀ የአፈርን ለምነት ለመጠበቅ ወይም ለማሻሻል የሚውል ቁስ ነው ፣

፬· "ፀረ ተባይ" ማለት ተዛማች ተባይን ሳይጨምር መደበኛ ተባይን ለመከላከል ፣ ወይም ለመቆጣጠር የሚውል የተቀመመ ነገር ፣ የዚሁ ድብልቅ ወይም ሕይወት ያለው የግብርና ግብዓት ነው ፣

፭· "ተባይ" ማለት ጥገኛ በሆነና ባልሆነ መልክ የሚኖሩ ህይወት ያላቸው ነፍሳት ፣ አረምና እፅዋት በሽታ ሆነው በማምረት ፣ በማቀነባበር ፣ በማከማቻ ፣ በማጓጓዝና በግብይት ሂደት በግብርና ምርቶችና ውጤቶች ላይ ጉዳት በማድረስ ምርቱና ጥራቱ እንዲቀንስ ምክንያት የሚሆኑ ሕይወት ያላቸው ነገሮች ናቸው ፣

፮· "ባለሥልጣን" ማለት ብሔራዊ የግብርና ግብዓት ባለሥልጣን ነው ፣

፯· "ሚኒስቴር" ማለት የገጠር ልማት ሚኒስቴር ነው ።

፫· <u>መቋቋም</u>

፩· ብሔራዊ የግብርና ግብዓት ባለሥልጣን /ከዚህ በኋላ "ባለሥልጣኑ" እየተባለ የሚጠራ/ የሕግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል ፣

፪· የባለሥልጣኑ ተጠሪነት ለገጠር ልማት ሚኒስቴር ይሆናል ።

፬· <u>ዋና መሥሪያ ቤት</u>

የባለሥልጣኑ ዋና መሥሪያ ቤት አዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች ይኖሩታል ።

፭· <u>ዓላማ</u>

የባለሥልጣኑ ዓላማ የሀገሪቱ የግብርና ግብዓቶች ምርት ፣ አቅርቦት ፣ ሥርጭትና ግብይት ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መንገድ መከናወኑን ማረጋገጥ ፣ በዘርፉም የአቅም ግንባታ ሥራን በመሥራት አምራቹንና ሸማቹን ኅብረተሰብ ተጠቃሚ ማድረግ ይሆናል ።

፮· <u>የባለሥልጣኑ ሥልጣንና ተግባር</u>

ባለሥልጣኑ ቀጥሎ የተመለከቱት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል ፣

፩· የአገሪቱን የገጠር ልማት ፖሊሲዎችንና እስትራቴጂዎችን መሠረት በማድረግ የግብርና ግብዓት ፖሊሲና እስትራቴጂ አዘጋጅቶ ያቀርባል ፣ ሲጸድቅም አፈጻጸሙን ይከታተላል ፣

፪· አግባብነት ካላቸው መሥሪያ ቤቶች ጋር ግንኙነት በመፍጠር የግብርና ግብዓት ሕጎች ተግባር ላይ እንዲውሉ ያደርጋል ፣

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "National Agricultural Input Authority Establishment Proclamation No. 288/2002."

2. *Definitions*

In this Proclamation, unless the context requires otherwise:

1) "Agricultural Input" means plant seed, fertilizer and pesticides available for market to improve production and productivity of the agricultural sector;
2) "Plant Seed" means a mature ovule or the seed, bulbs, tubers, cutings, or any other plant material used for the propagation of plants;
3) "Fertilizer" means any natural or industrial product of organic or inorganic origin that contain one or more plant nutrient which could help to maintain and/ or improve soil fertility;
4) "Pesticide" means any substance, chemical, compound or mixture thereof or a living organism intended for use as an agricultural input to prevent or control regular pests excluding migratory pests;
5) "Pest" means a free, parasitic or saprophytic, which cause a decline in yield and quality during production, processing, storage, transport and marketing of agricultural produces and commodities;
6) "Authority" means the National Agricultural Input Authority;
7) "Ministry" means the Ministry of Rural Development.

3. *Establishment*

1) The National Agricultural Input Authority (hereinafter referred to as the "Authority") is hereby established as an autonomous body of the Federal Government;
2) The Authority shall be accountable to the Ministry of Rural Development.

4. *Head Office*

The head office of the Authority shall be in Addis Ababa, and it may have branch offices as required.

5. *Objective*

The objective of the Authority is to ensure that the production, supply, distribution and marketing of agricultural inputs is undertaken in efficient and effective manner, and capacity is built in the sector to benefit producers and the user community.

6. *Powers and Duties of the Authority*

The Authority shall have the powers and duties to:

1) formulate agricultural input policy and strategy based on the national rural development policies and strategies, and upon approval, follow up the implementation thereof;
2) effect the implementation of agricultural input laws by establishing links with appropriate institutions;

፫· ለግብርና ግብዓት ግምገማና ማጽደቅ የሚረዱ መመሪያዎችንና የአሠራር ሥርዓቶችን ያወጣል ፣ ሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል ፣

፬· የሀገሪቱን የልማት ፍላጎት መሠረት ያደረጉ የግብርና ግብዓት ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች እንዲዘጋጁ የሚያስችሉ መመሪያዎችና የአሠራር ሥርዓት ያወጣል ፣

፭· አግባብነት ያላቸው ሕጎች እንደተጠበቁ ሆነው ፣ ወደ ሀገር ውስጥ ለሚገቡም ሆነ ወደ ውጭ ለሚላኩ የግብርና ግብዓቶች ይለፍ ፈቃድ ይሰጣል ፣

፮· የግብርና ግብዓት ጥራቱ ተጠብቆ ለተጠቃሚው መሠራጨቱን ያረጋግጣል ፣

፯· የግብርና ግብዓት ኢንዱስትሪውን ለማሳደግ እንዲረዳ የገበያ ፍላጎት ትንበያ ጥናት ያካሂዳል ፣

፰· የግብርና ግብዓቶች ዋጋን ለማረጋጋት የሚጠቅሙ ጥናቶችን በማካሄድ በመንግሥት መወሰድ ስለሚገባቸው እርምጃዎች የውሳኔ ሐሳብ ያቀርባል ፣

፱· የግብርና ግብዓት ምርት ፣ አቅርቦትን ፣ ሥርጭትንና ግብይትን አቅም ለመገንባት አስፈላጊውን እገዛ ያደርጋል፣

፲· የግብርና ግብዓት ኢንዱስትሪውን ልማት ለማፋጠን እንዲረዳ በሕዝቡ ዘንድ ትክክለኛ ግንዛቤ እንዲኖር አስፈላጊውን ያደርጋል ፣

፲፩ ባለሀብቶች በግብርና ግብዓቶች ምርትና ሥርጭት ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ያበረታታል ፣

፲፪· የግብርና ግብዓቶች እጥረትን ለመሸፈን እንዲረዳ አግባብ ካላቸው መ/ቤቶች ጋር በመተባበር የአቅርቦቱን አስተማማኝነት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣

፲፫· ማዕከላዊ የግብርና ግብዓት መረጃና የኢንፎርሜሽን ሥርዓት ያቋቁማል ፣

፲፬· ውል ይዋዋላል ፣ ይከሳል ፣ ይከሰሳል ፣ የንብረት ባለቤት ይሆናል ፣

፲፭· በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ለሚሰጠው አገልግሎት ክፍያ ይሰበስባል ፣

፲፮· ዓላማውን ከግብ ለማድረስ አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ተመሳሳይ ተግባራትን ያከናውናል ።

፯· ድርጅታዊ አቋም

፩· በመንግሥት የሚሾም አንድ ዋና ሥራ አስኪያጅ ፣ እና

፪· አስፈላጊ ሠራተኞች ፣

ይኖሩታል ።

፰· የዋና ሥራ አስኪያጁ ሥልጣንና ተግባር

የባለሥልጣኑ ዋና ሥራ አስኪያጅ በመንግሥት የሚሾም ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል ፤

፩· በዚህ አዋጅ አንቀጽ (፮) ላይ የተጠቀሱትን የባለሥልጣኑን ሥልጣንና ተግባራት በበላይነት ይመራል ፣ ይፈጽማል ፣

፪ የባለሥልጣኑን ዓመታዊ የሥራ ፕሮግራምና በጀት በማዘጋጀት ለገጠር ልማት ሚኒስቴር ያቀርባል ፣

፫· በመንግሥት የፀደቀው በጀት በሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል ፣ ያረጋግጣል ፣

፬· በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎች መሠረት የባለሥልጣኑን ሠራተኞች ይቀጥራል ፣ ያስተዳድራል ፣ ያሰናብታል ፣

፭· ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ባለሥልጣኑን ይወክላል ፣

፮· ለባለሥልጣኑ በተፈቀደለት በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል ፣

፯· እንደአስፈላጊነቱ ለሌሎች የባለሥልጣኑ ሠራተኞች ውክልና ይሰጣል ፣

3) issue guidelines and procedures for agricultural input evaluation and release, and monitor their implementation;

4) issue guidelines and procedures for the proper formulation and preparation of agricultural inputs programs and projects in line with the development requirement of the country;

5) without prejudice to relevant laws issue import and export permit for agricultural inputs;

6) ensure the distribution of high quality agricultural input to users;

7) provide the necessary assistance with respect to market and demand forecast studies in order to enhance the development of the agricultural input industry thereof;

8) undertake studies and submit recommendations to the government to take necessary actions to stabilize the price of agricultural inputs;

9) make the necessary support in capacity building in production; supply; distribution and marketing of agricultural input;

10) promote proper public awareness to enhance the growth and development of the agricultural input industry;

11) encourage the private sector to actively participate in the production and distribution of agricultural inputs;

12) facilitate and ensure; in cooperation with relevant organizations; the supply and a availability of agricultural inputs to help cover shortages;

13) establish a central agricultural input data and information system;

14) enter into contracts, sue and be sued, own properties;

15) collect fees for services rendered as per developed guideline;

16) perform such other similar duties necessary to achieve its objectives;

7. *Organizational Structure*

The Authority shall have:

1) A General Manager to be appointed by the Government, and

2) the necessary staff.

8. *Powers and Duties of the General Manager*

The General Manager shall be appointed by the Government and shall have the following powers and duties:

1) cause the execution of powers and duties of the Authority as stated in Article 6 of this Proclamation;

2) prepare and submit the work program and budget of the Authority to the Ministry of Rural Development;

3) execute and follow-up the implementation of the budget approved by the Government;

4) employ, administer and dismiss employees of the Authority in accordance with the Federal Civil Service laws;

5) represent the Authority in its relations with third parties;

6) effect expenditure in accordance with the budget and work program approved for the Authority;

7) delegate, when necessary, to other staff of the Authority;

፰· የባለሥልጣኑ የሥራ አፈጻጸምና የሂሣብ ሪፖርት አጠናቅሮ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል ፤

፱· ከሚኒስቴሩ የሚሰጡ ሌሎች ተጨማሪ ተግባራትን ያከናውናል ።

፱· <u>በጀት</u>

የባለሥልጣኑ በጀት ከሚከተሉት ምንጮች የሚገኝ ይሆናል ፤

፩· ከመንግሥት የሚመደብ በጀት ፤

፪· ከተለያዩ ምንጮች ከሚገኙ ዕርዳታዎችና ስጦታዎች ።

፲· <u>ስለሂሣብ መዛግብት</u>

፩· ባለሥልጣኑ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብት ይይዛል ፤

፪· ባለሥልጣኑ የሂሣብ መዛግብትን ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ በዋናው ኦዲተር ወይም ዋናው ኦዲተር በሚሰይመው ሌላ ኦዲተር እንዲመረመሩ ያደርጋል ።

፲፩· <u>የተሻሩና ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች</u>

፩· የሚከተሉት ሕጎች በዚህ አዋጅ ተሽረዋል፤

ሀ) የብሔራዊ የዕፅዋት ዘር ኢንዱስትሪ ድርጅት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፶፮/፲፱፻፹፭ /እንደተሻሻለ/።

ለ) የብሔራዊ የማዳበሪያ ኢንዱስትሪ ኤጀንሲ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፩፻፮/፲፱፻፹፮ /እንደተሻሻለ/ ።

፪· ይህን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም ሕግ ወይም መመሪያ በዚህ አዋጅ ውስጥ የተካተቱ ጉዳዮችን በሚመለከት ተፈጻሚነት አይኖረውም ።

፲፪· <u>ስለመብትና ግዴታ መተላለፍ</u>

፩· በአዋጅ ቁጥር ፶፮/፲፱፻፹፭ /እንደተሻሻለ/ ተቋቁሞ የነበረው ብሔራዊ የዕፅዋት ዘር ኢንዱስትሪ ድርጅት መብትና ግዴታ እንዲሁም በዕፅዋት ዘር አዋጅ ቁጥር ፪፻፮/፲፱፻፺፪ ለድርጅቱ ተሰጥቶ የነበረው ሥልጣንና ኃላፊነት በዚህ አዋጅ መሠረት ለባለሥልጣኑ ተላልፏል ፤

፪· በአዋጅ ቁጥር ፩፻፮/፲፱፻፹፮ /እንደተሻሻለ/ ተቋቁሞ የነበረው የብሔራዊ የማዳበሪያ ኢንዱስትሪ ኤጀንሲ መብትና ግዴታ እንዲሁም በማዳበሪያ ማምረትና ንግድ አዋጅ ቁጥር ፩፻፴፯/፲፱፻፺፩ ለኤጀንሲው ተሰጥቶ የነበረው ሥልጣንና ኃላፊነት በዚህ አዋጅ መሠረት ለባለሥልጣኑ ተላልፏል ።

፲፫· <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከሰኔ ፴ ቀን ፲፱፻፺፬ ዓ·ም· ጀምሮ የፀና ይሆናል ።

አዲስ አበባ ሰኔ ፴ ቀን ፲፱፻፺፬ ዓ·ም·

ግርማ ወልደጊዮርጊስ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት



8) submit, to the Ministry, the performance and financial report of the Authority;

9) perform other duties assigned by the Ministry.

9. *Budget*

The budget of the Authority shall be drawn from the following sources:

1) budget allocated by the government;
2) donations and grants from different sources.

10. *Book of Accounts*

1) The Authority shall keep complete and accurate book of accounts.
2) The Authority shall cause the audit of its accounts; at least once in a year; by the Auditor General or by an auditor delegated by him.

11. *Repealed and Inapplicable Laws*

1) The following laws are hereby repealed:
   (a) National Seed Industry Agency Establishment Proclamation No. 56/1993, (as amended);
   (b) National Fertilizer Industry Agency Establishment Proclamation No. 106/1994, (as amended;)
2) Any other law or directive which is inconsistent with this proclamation shall not be applicable on matters provided in this Proclamation.

12. *Transfer of Rights and Obligations*

1) The rights and obligations of the National Seed Industry Agency established under Proclamation No. 56/1993 (as amended), as well as the powers and duties entrusted to the Agency under Seed Proclamation No. 206/2000 are hereby transferred to the Authority;
2) The rights and obligations of the National Fertilizer Industry Agency established under Proclamation No. 106/1994 (as amended), as well as the powers and duties entrusted to the Agency under fertilizer manufacturing and trade Proclamation No. 137/1998 are hereby transferred to the Authority.

13. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 7th day of July, 2002.

Done at Addis Ababa, this 7th day of July, 2002.

*GIRMA W/GIORGIS*
*PRESIDENT OF THE FEDERAL*
*DEMOCRTIC REPUBLIC OF ETHIOPIA*

<u>ማረሚያ ቁጥር ፩/፲፱፻፺፬</u>

የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር ፪፻፹፮/፲፱፻፺፬ የሚከተሉት እርማቶች ተደርገውበታል፤

1· አንቀጽ ፲፫፤ (መ) "ከገቢ" ከሚለው ቀጥሎ "ግብር" የሚል ቃል ተጨምሮ ይነበብ።

2· አንቀጽ ፹፯ ከንዑስ አንቀጽ (፪) (ሀ) ቀጥሎ፤ "ለ) ፳ ሺ ብር" የሚል ተጨምሮ ይነበብ።

## Corrigendum No. 1/2002

The "Five (5) years" after the word "next" in sub-Article (1) of Article 28 of the Income Tax Proclamation No. 286/2002 shall read "three (3) years."

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE